# "ያልጸዳችው አጽጂ"

መቅደስ መበዓ
(mkds.alem@gmail.com)

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ስም ሕጋዊ መጠሪያዬ ሲሆን ይህንን ያደረግሁት በብዕር ስም ባለማመን ሳይሆን፣ ሰዎች ይዘውት እንደሚቀርቡት ርዕሰ ጉዳይ ማንነታቸውን መደበቅ ወይም መግለጥ እንደሚኖርባቸው በብርቱ ስለማምን ነው፡፡ እኔ በግሌ ከላይ በተገለጸው ርዕስ በብዕር ስም የጻፉትን ወንድሞቻችንን ድርጊት እቃወማለሁ፡፡ ምንም እንኳ ስማቸውን ያልገለጹት የሚያመጣላቸውን ዝናና ዕውቅና ሽሽት ብቻ እንደ ሆነ ቢገልጹም አሳማኝ ሆኖ ግን አላገኘሁትም፡፡ ማስረጃዬን ማጠቃለያ በሚለው ርዕስ ሥር አቀርባለሁ፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳችን እርስ በርሳችን እንድንተያይ እንዲሁም የተሳሳተን ሰው በየዋሐት መንፈስ እንድናቀና ያስተምረናል፡፡ ክርስትና ወደ ፍጽምና የሚደረግ ጉዞ በመሆኑ ለዚሁ ሲባል የሚደረግ ሂስ መሰጣጠት በራሱ ምንም ክፋት የለበትም፡፡ አንድ አንኳር እውነት ቢኖር እግዚአብሔር የየትኛውንም ድርጊት መነሻ ሐሳብ (motive) ማየቱን ነው፡፡

ይህንን እውነት መሠረት በማድረግ በጌሜም መጽሔት ቁጥር 13 ላይ "ማቅናት? ወይስ ንቀት?" ለሚለው ጽሑፍ ጸሐፊዎች ጥያቄና አስተያየት እንደሚከተለው ለማቅረብ ሞክሬያለሁ፡፡ በተጨማሪም ወንድሞች ሲጯጯኹ እዚያው ቤት ውስጥ ያለ ሌላ ወንድም (መጽሐፍ ቅዱስ አማኞችን በሙሉ ወንድሞች ስለሚል እንጂ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ሴት መሆኔን ልብ ይሏል) ባይተዋርነት ካልተሰማው በስተቀር ዝም አይልም፡፡ የኢትዮጵያዊነት ባሕላችንም ቢሆን "አንተም ተው፤ አንተም ተው" ብሎ ይዳኛል፡፡

ይህ ጹሑፍ ሁለት ክፍሎች አሉት፤ የመጀሪያው ለ"ማቅናት? ወይስ ንቀት?" ጸሐፍት ወንድሞቻችን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለጌሴም መጽሔት ዝግጅት ክፍል ነው፡፡

## "ደግ ደጉን"

ጽሑፋችሁን ሚዛናዊነት ለማስያዝ በጣም መጣራችሁ ስለ ጳውሎስ ፈቃዱ ያቀረባችሁት ምስክርነት ምስክር ይሆናችኋል፡፡ ለምሳሌ የእርሱን መልካምነት በመግለጽ አሁን ካለው ትውልድ መሐል በበጎ ሥራቸው ከሚጠሩት ተርታ አሰልፋችሁታል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ሥራዎቹም ለቤተ ክርስቲያን በረከት እንደ ሆኑ ገልጻችኋል፡፡

አባቶች ህጻጽ አልባ እንዳልሆኑም ሰው ሁሉ ድካም እንዳለበት መጻፋችሁም ለሚዛናዊነት የመጣራችሁ ሌላው አብነት ነው፡፡ (ሰው የሚለው ጎራ ደግሞ የሁላችንም መገናኛ መሆኑ ይጤንልኝ፡፡)

ከዚህም በተጨማሪ ቅሬታ እያላችሁ ምንም እንዳልተሰማው ሰው አርፋችሁ ሳትቀመጡ ቅሬታችሁን መግለጻችሁ ቢያንስ በእኔ እምነት ትልቅ ነገር ነው፡፡

## ጥያቄ ለጸሓፊ ወንድሞቻችን

ማንነታችሁን መግለጽ የማትፈልጉት በታዋቂ ሰዎች ላይ በመጻፍ የሚገኝ ዝና ስለማትፈልጉ ብቻ እንደሆነ ገልጻችኋል፡፡ በእናንተ እምነት በታዋቂ ሰው ላይ የጻፈ ማንኛውም ሰው እንዲሁ ስለ ጻፈ ብቻ ዕውቅናን ያተርፋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የዓላማ



www.Ethiocross.com

መር መጽሐፍ ደራሲ መጋቢ ሪክ ዋረን በዓለማችን ውስጥ ስማቸው የናኘ ደራሲ እና መጋቢ ናቸው። አንድ ሌላ ኢትዮጵያዊ መጋቢ የሪክ ዋረን ዓላማ መር መጽሐፍ ስሕተት እንደ ሆነ፣ እንዳውም ከጨለማው ዓለም ጋር ተያያዥነት እንዳለው መጽሐፍ ጽፈው አሳትመዋል፤ እኝህ ሰው ታዋቂ ናቸው? ሥራቸውስ በምን ያህል ቋንቋ ተተርጉሞአል?

ጳውሎስ መጋቢ ዳንኤልን ለማናገር ሙከራ አድርጓል፤ ምንም እንኳ የጠበቀው ጊዜ በቂ እንዳልሆነ ብታምኑም። እናንተ ከጳውሎስ ጋር በጉዳዩ ለመነጋገር እንዳልሞከራችሁ ከራሱ ጋር ባደረግሁት ኢመደበኛ ቃለ ምልልስ ተገንዝቤአለሁ። ለምን አግኝታችሁ ልታናግሩት አልሞከራችሁም?

ወንድም ጳውሎስ ፈቃዱ ከመጋቢ ዳንኤል መኮንን ጋር ስለ ጉዳዩ ከበዓለ ሢመቱ በፊትም ቢሆን ለመነጋገር በቤተ ክርስቲያኒቷ የሕዝብ ግንኙነት ኀላፊ በኩል ተደጋጋሚ ጥያቄ ማቅረቡንና ነገር ግን ጥረቱ ያለመሳካቱን ይገልጻል። በተጨማሪም መጋቢ ዳንኤል መኮንንን አግኝቶ ማናገር አስቸጋሪ እንደ ሆነ ህዳር 2001 "የኅብረት ያለህ!" በሚል ርዕስ ፊቸር ጽፈው የነበሩ ወንድሞች እና በጥቅምት 2002 "ጥያቄ ያስነሣው 'ሐዋርያዊው' በዓለ ሢመት" በሚል በማቴቴስ መጽሔት የወጡ ጽሑፎች ዋቢ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጽሑፋችሁ ውስጥ "እኛም እንዳንተ ጠሪ አክባሪ ብለን …" ስትሉ በመስከረም ሁለቱ በዓለ ሲመት መገኘታችሁን ታስነብቡና ትንሽ እልፍ ብላችሁ ደግሞ "መቼም እየተሳለቅህም ቢሆን ጠሪ አክባሪ ብዬ ብለህ …" ስትሉ የመጀመሪያውን አባባላችሁን የሚያደፈርስ ገለጻም ታክላላችሁ። "እኛም እንደ አንተ ጠሪ አክባሪ ብለን …" ብላችሁ ሐሳቡንም ተጋርታችሁ አልነበረ እንዴ? ቆየት ብላችሁ ለምን ሐሳባችሁን ቀየራችሁ? ወይስ እናንተም "መሳለቃችሁ" ነበር?

ጹሑፋችሁን ያቀረባችሁት ታሪካዊ ኀላፊነታችሁን ልትወጡ እንደ ሆነ ገልጻችኋል። ከታሪክ አንጻር የእናንተን አጻያፊ ስድብስ እንዴት ተመለከታችሁት? ታሪክ ላንዱ ወገን አድልቶ መሳደብ ይፈቅዳል እንዴ?

ቅድስት ዳንኤል (የመጋቢ ዳንኤል ልጅ) ጳውሎስ ስለ አባትዋ የጻፈውን ስታነብ ምን ሊሰማት እንደሚችል ጳውሎስ እንዲገምት ጠይቃችኋል። ጉዳዩ የስሜት ከሆነ፣ እስኪ እኔም መልሼ ደግሞ ልጠይቃችሁ። የጳውሎስ አባትስ "ወጥ እረገጥ፣ ስድ፣ ክፍት አፍ፣ ጥራዝ ነጠቅ፣ ትንሽ፣ ተራ …" እያላችሁ ስትሰድቡት ምን ሊሰማቸው እንደሚችል እናንተስ ገምታችኋል?

እንደ እውነቱስ ከሆነ እውነቱንና የተደረገውን ነገር ወይስ "እገሌን ምን ሊሰማው ይችላል?" እያልን ለሰው ፊት እያደላን መጻፍ ነው ያለብን? ለእውነት የወገነ ሰው አብሮ የወዳጅ ዘመዱን ስሜት ሁልጊዜ ሊያስተናግድ አይችልም።

"አባት" የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የሚያገለግለው በዕድሜ ለገፉት ብቻ ነው እንዴ? ጢሞቴዎስ በዕድሜው ልጅ የነበረ አባት ነው። ጳውሎስን "ለዕድሜ እኩዮችህ እንኳን የማይመጥን ስድብ …" ብላችሁታልና፤ ጢሞቴዎስ "ለዕድሜ እኩዮቹ የሚመጥን ስድብ" መሳደብ ተፈቅዶለታል? ይህንን የምጠይቃችሁ እግዚአብሔር በጳውሎስ እንደሚሠራ እንደምታምኑ ስለጻፋችሁ ነው።

አባቶች ህጸጽ አልባ እንዳልሆኑ እናንተም ብትሆኑ በእነርሱ ማዘናችሁን፣ መሰናከላችሁን … ገልጻችኋል። ታዲያ ምነው ለሌላው ሰው ህጸጽ እስክትስቱ ድረስ አስገረማችሁ? በእነርሱ ተግባር ባዘናችሁ ጊዜስ ስሜታችሁን የገለጻችሁበት መንገድ ምን ነበር?


www.Ethiocross.com

ወንድማችን ጳውሎስ ሐሳቡን እንዲያደረጅለት የዶ/ር ዘማሪ ደረጀ ከበደን መዝሙር መጠቀሙን "በምን ሥልጣን" እንዳደረገው ትጠይቃላችሁ፤ እስኪ እኔም መልሼ ልጠይቃችሁ። ጥያቄው የሥልጣን ከሆነ እናንተስ የዚሁ ወንድማችንን መዝሙር (ጸልይለት ለደከመ) የሚለውን በምን ሥልጣን ነው በጽሑፋችሁ ውስጥ ለፈለጋችሁት ሐሳብ የተጠቀማችሁት?

በመሠረቱ አንድ በህትመትም ሆነ በማናቸውም መልኩ ለሕዝብ የቀረበን ሥራ ምንጭ ጠቅሶ መጠቀም አግባብ ሲሆን፣ ሌላ የሚያስነሣው የሥልጣን ጥያቄ ግን የለም።

ስለ ልጁ ማንነት ስታወሩን "ተራና ትንሽ" ብላችኋል። በምን መለኪያ ነው አንድ በጌታ ያመነ ወንድም "ትንሽ" የሚባለው? በአንጻሩ ደግሞ "ትልቅ" የሚባለውስ?

የ"ማቅናት? ወይስ ንቀት?" ጸሐፍት ወንድሞቼ እናንተም ልክ እንደ ጳውሎስ ጥያቄ፣ ቅሬታና ግርታ እንዳላችሁ (የመስከረሙን በዓለ ሢመት ጨምሮ) ገልጻችኋል። ለምሳሌ "አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ለዘላለም ካህን ነህ" ተብሎ በወቅቱ የተሰነዘረው ሐሳብ ለእናንተም ግልጽ አይደለም። ይህንን ሐሳባችሁን ለአባቶች በምን መንገድ ነው የምታሳውቋቸው?

በጣም የሚገርመው ለአባቶች በሰነዘራችሁት ምክር እንደ ጳውሎስ ያሉ ጥያቄ ያለባቸውን ወጣቶች እንዲቀርቡ ታበረታታላችሁ። ምነው እናንተስ ጥያቄ አለን ስትሉ አልነበረ እንዴ? ባጠቃላይ ከዚህ መረዳት የሚቻለው እናንተ በሰው ጀርባ ሆናችሁ ጥያቄያችሁን የምታቀርቡ እንጂ በጠየቃችሁት ጥያቄ ለሚመጣባችሁ ተጠያቂነት የተዘጋጀ ማንነት እንደሌላችሁ ነው። እዚህ ጋር ስማችሁን ያለመጥቀሳችሁን ምክንያት መገመት ይቻላል፤ ያው ተጠያቂነትን ሽሽት!

ወንድም ጳውሎስ ፈቃዱ ስለ ሁሉ ነገር መልስ ለመስጠት እንደሚደፍር ጽፋችኋል። ከጽሑፉ ላይ ልጥቀስ፤ "በዚህ ጽሑፌም ነገረ መለኮታዊ ሙግቱን በጥልቅ ለማንሣት አልሞክርም። በዚህ ጉዳይ ምሁራኑ የሚሉትን ለመስማት ከአንባቢዎቼ ጋር አብሬ እጠብቃለሁ።" _የነጻነት መዘዝ_ ገጽ 1። ይህንን ዐረፍተ ነገር አላነበባችሁትም? እውን ይህ ወንድም ስለ ሁሉ ነገር ደፍሮ ይናገራል?

## <u>እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ሐሳቦች</u>

በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ በሰጣችሁት ማብራሪያ "የነጻነት መዘዝ" በሚል ርእስ ለጻፈው ጽሑፍ "ታሪካዊ ኃላፊነታችሁን" ለመወጣት እንደ ጻፋችሁ ገለጻችሁ፤ ጥቂትም እልፍ ሳትሉ ደግሞ ይኸው ወንድም እስከ ዛሬ "ለጮኸው ጩኸት" እንደ ሆነ የምትጮኹት ገልጻችኋል። እዚህ ላይ ሁለት የምክንያት ግጭቶች ይታያሉ። ስለዚህ ከእነዚህ የምክንያት ግጭቶች መረዳት የሚቻለው እውነት "የነጻነት መዘዝ" በሚለው ጽሑፍ ሽፋን የቆየና የተደበቀ ስሜታችሁን ማውጣታችሁን ነው።

"ደግ ደጉን" በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር የልጁን መልካምነት ለመመስከር በአሁኑ ሰዓት ካሉ ወጣት ክርስቲያኖች መካከል በጽሑፍ ሥራው ተጠቃሽ እንደ ሆነ አለመጥቀስ አግባብ እንዳልሆነ የዚህም ዋቢ <u>በአሁኑ ጊዜ</u> (ሰረዝ ከራሴ) በተለያዩ መጽሔቶች የሚወጡ ጽሑፎቹ እንደሆኑ ትገልጻላችሁ። ጳውሎስንም ሆኖ መፈጠር እንደሚያስመኝ ታክላላችሁ። በቀጣዩ አንቀጽ ደግሞ በእነዚሁ (<u>በአሁኑ ጊዜ</u> (ሰረዝ ከራሴ) በተለያዩ መጽሔቶች በሚወጡ ጽሑፎቹ) የልጁን ነውራምነት (በእናንተ ገለጻ ክፍት-አፍነት) ምስክር ታደርጓቸዋላችሁ። እነዚህ በአሁኑ ጊዜ የሚወጡ ጽሑፎቹ የስንቱ ምስክር ናቸው? አንድ ጠበቃ የከሳሽም


www.Ethiocross.com

የተከሳሽም ጠበቃ መሆን አይችልም፡፡ ለሁለት ተጻራሪ ሐሳብ አንድ ምስክር አይቆምም፡፡ (ወንድማችን ጳወሎስ ከአንድ ዓመት ወዲህ በተለያዩ መንፈሳዊ መጽሔቶች ላይ የጻፋቸውን ጽሑፎች ከአጭር የይዘት ማብራሪያ ጋር ከዚህ በታች ማየት ይቻላል)

በጽሑፋችሁ ውስጥ "እኛም እንዳንተ ጠሪ አክባሪ ብለን …" ስትሉ በመስከረም ሁለቱ በዓለ ሢመት መገኘታችሁን ታስነብቡና ደግሞ ትንሽ እልፍ ብላችሁ መጠራትህን እንጠራጠራለን ትላላችሁ፡፡ "የነጻነት መዘዝ" በሚለው ጽሑፍ የመጀመሪያ ገጽ ላይ "ለእኔ የደረሰኝ የጥሪ ካርድ ላይ …" የሚል ሐረግ አለ፡፡ በመጠራቱ ሳታምኑበት ነው ሐሳቡን የተጋራችሁት?

ከዚህ የከፋው ደግሞ አንድ መጠራቱን በምስክር የገለጸን ሰው ሳትጠራ ይመስላል በግብዣው ላይ የተገኘሽው ማለት የግለ ሰቡን ማንነት ማጠልሸት (character assassination) ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ ወንድም ያላችሁን ከልክ ያለፈ ጥላቻ ያሳያል፡፡

ከዚሁ ከጥርጥር ርእሰ ጉዳይ ሳንወጣ "ደግ ደጉን" በሚለው ንዑስ ርእስ ሥር ምነው እሱን ባደረገኝ ስትሉ አሞካሻችሁት፤ ቀጠል ሲል ደግሞ "በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ሰዎች መካከል በድፍረትና ባለአዋቂነት አንተን የሚስተካከል መኖሩን ተጠራጥረናል" ትላላችሁ፡፡ ያለ ምንም ጥርጥር በድፍን ኢትዮጵያ የባለጌ ምሳሌ እና እርሱን ሆኖ መፈጠር የሚሉት ሐሳቦች እርስ በእርሳቸው ይላተማሉ፡፡

## <u>አልሸሹም ዘወር አሉ</u>

የበዓለ ሢመቱ ዕለት ጳውሎስ ከጎኑ ከነበረ ሰው ጋር ከመጀመሪያው ጀምሮ ይሟሟቅ እንደ ነበር ስትከታተሉ መዋላችሁን ገልጻችኋል፡፡ እናንተም ከመጀመርያው አንሥቶ እርሱን ትከታተሉ ነበረ ማለት ነው፡፡ ይህ አንድ ዐይነት ስሕተት ነው፡፡ የሁለታችሁም ግንኙነት ወደ ላይ ሳይሆን ወደ ጎን ነበረ ማለት ነው፤ እርሱ ካጠገቡ ከተቀመጠው ሰው ጋር፣ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር፤ ይህ በከሰሱት ወንጀል መልሶ ተከሳሽ ያደርጋል፡፡

ከጳውሎስ በተለየ መልኩ የእግዚአብሔርም ሕልውናም እንደ ተሰማችሁ ገልጻችኋል፡፡ ሰው በእግዚአብሔር ሀልዎት ተውጦ ሌላውን ሰው ሊከታተል አይችልም፡፡

"የነጻነት መዘዝ" በጨዋ ቋንቋ እንዳልተጻፈ ኮነናችሁት፤ ወንድማችንን "… ጆርባ ላይ የተጣበቀ ቅማል፣ ተራ፣ ትንሽ፣ ስድ፣ ወጥ እረገጥ፣ አጉራ ዘለል …" የሚሉ ቃላትን እየተጠቀሙ መንቀፍስ ምድቡ ከ"ጨዋ ቋንቋ" መሆኑ ነው?

ለአንድ መንፈሳዊ ሥራ ዓለማዊ (secular) ሥራን መጠቀም በራሱ ምንም ክፋት የለውም፡፡ (የሥራው ዐይነት፣ የተጠቀምንበት ዓላማ፣ የምንጠቅስበት መንገድ፣ የምንጠቅስበት ጉዳይ እና የመሳሰሉትን ከግምት ማስገባት ሳንረሳ)፡፡ ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ም.17 ላይ ከዓለማዊ (secular) ጠቅሶ ተናግሯል፡፡

እናንተ ግን ወንድማችን በአዲስ ነገር ጋዜጣ የወጣን ጽሑፍ መጠቀሙን ጉዳዩንም መንፈሳዊ መልክ ሊያሲዘው መሞከሩን ትኮንናላችሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ጽሑፎች በዓለማዊ ሥራዎች ላይ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ አንዳንዴ አንድ ጽሑፍ በሁለቱም ዓለማት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በታች የቀረበው ግጥም ማቴቴስ በተሰኘው መንፈሳዊ መጽሔትና አዲስ አድማስ በተባለው ዓለማዊ ጋዜጣ ላይ ታትሞ ወጥቷል፡፡


www.Ethiocross.com

## እረኛውና በጎቹ

ያ
መልካም እረኛ
"በጎቼ
ድምፄን ይሰማሉ፤
ከሌሎቹ ድምፅ መሐል
የእኔን ድምፅ ያውቃሉ"
ብሎ ነበር ያኔ።
አሁን ግን በጎቹ
ድምፁን ከቶ አይሰሙም፤
ከድምፆችም መኻል
የእሱን ድምፅ አይሰሙም፤
ዛሬም የእረኛው ድምፅ
ፍጹም ሳይለወጥ
ያው ነው እንደነበረ
እረኛው አላወቀም
የበጎቹ ጆሮ እንደ ተቀየረ። [1]

እንዳጋጣሚ ሆኖ ይህም ግጥም የተጻፈው ያንኑ የመስከረም ሁለቱን በዓለ ሢመት በሚመለከት ነው፤ ገጣሚው በጽዋ አዳራሽ በተካሄደው ዝግጅት ላይ ነበሩ።

የ"ማቅናት? ወይስ ንቀት?" ጸሐፍት ወንድሞቻችን፣ ሐሳባችንን ያጎለብታል ስትሉ እናንተስ የደበበ ሰይፉን ዓለማዊ (secular) ግጥም መጠቀማችሁን ረሳችሁት? (ስለዚህ ግጥም በሌላ ርእስ ሥርም እመለስበታለሁ።)

## ፎቶ መለጠፍ

"የነጻነት መዘዝ" የሚለውን ጽሑፍ በተሳሳተ መንገድ እንደተረዳችሁት ከሚያሳዩት ቦታዎች መካከል ፎቶ የመለጠፍና መስቀል የመሸከም ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው። ከጽሑፉ ልጥቀስ፣

> በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የመጋቢውን ምስል ማተም መጋቢውን ከማስተዋወቅ ውጭ ክርስቶስን ኢየሱስን የመግለጥ አቅሙ አነስተኛ ነው። መጋቢው ይህ የተደረገላቸው ራሳቸው ባከናወኑት ሥራ ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር፤ አሊያ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሁልጊዜም የምትወከለው በእሳቸው ፎቶ ነው ማለት ነው?" (ሰረዝ ከራሴ)።

የጽሑፉ ሐሳብ የመጋቢው ፎቶ በየቦታው መብዛቱን ነው የሚያወሳው። ታዲያ ይህ አባባል ትክክል አይደለምን? "ይህ የተደረገላቸው [ፎቶ በየቦታው እየታተመ የተሰራጨላቸው] <u>ራሳቸው ባከናወኑት ሥራ</u> [መጽሐፍ ጽፈው፣ ወዘተ] ቢሆን ኖሮ ይሻል ነበር" ማለት ፎቶ አታውጡ ማለት አይደለም። የሆንኩትን ሁሉ የሆንኩት በእግዚአብሔር ጸጋ ነው፣ እንዳለው ሐዋርያው ጳውሎስ ያተለቀንን ጌታ እንዳንሸፍነው ለማለት እንጂ ፎቶ መለጠፍ ስህተት ነው ለማለት አይደለም የቀረበው።


www.Ethiocross.com

ወንድሞቼ "አሁን ፎቶ ከመለጠፍ የከፋ ስህተት ጠፍቶ ነው?" ስትሉስ የጠየቃችሁት መጀመሪያውንስ ቢሆን እርሱ "ፎቶ መለጠፍ ስሕተት ነው" ብሎ መቼ ጻፈ? "ራሳቸው ባከናወኑት ሥራ" የሚለው ሐረግ እንደሚያስረዳው በእርሳቸው ለተሠራው ሥራ ባለቤቱ ሌላ ስለሆነ የፎቷቸው እዚህም እዚያም መለጠፍ ባለቤቱን እንዳይሸፍነው በሚል ሥጋት የተሰነዘረ ሐሳብ ነው፡፡

ጳውሎስ በቅርብ ጊዜ ሥራዎቹ ላይ ምስሉን እንዳላያያዘ ከመጽሐፎቹ ማየት ይቻላል ("የወዳጅ ፍላጻ" እና "ያልተንኳኩ በሮች" በቅርቡ ያሳተማቸው ሥራዎቹ ሲሆኑ ፎቶ የላቸውም፤ "የእምነት ኀይል" ለ3ኛ ጊዜ ዘንድሮ ሲታተም በፊት የነበረው ፎቶ እንዲጠፋ ተደርጎ ነው)፡፡ ለመሆኑ የተቻችሁት የነጻነት መዘዝ የተሰኘው ጽሑፉ የጸሐፊው ፎቶ ነበረው? ከተለያዩ መጣጥፎቹ ጋር ፎቶዎቹ በተለያዩ መጽሔቶች ላይ መውጣታቸው ግን እውነት ነው፤ ሆኖም የመጽሔቶቹ አሳታሚ እርሱ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ታዲያ በባለ መጽሔቶች ድርጊት ("ስሕተት") እርሱ ሊኮነን ይገባል? የሆነ ሆኖ ፎቶውን ቢያይዝ እንኳ "ራሱ ባከናወነው ሥራ" እንጂ ሌላ ተቋምን (ቤተ ክርስቲያንን) በመወከል አይደለምና በእርሱ ሙግት መሠረት ከእናንተ ክስ ነጻ ይሆናል፡፡

"በእሳት የጋለው የብረት መስቀል አንድ ጊዜ በመጋቢው ጫንቃ ላይ ሆኖ ለማየት መጓጓትህ" በማለት ገልጻችኋል፡፡ ከየት አመጣችሁት? ጉዳዩን እስኪ ከጽሑፉ በቀጥታ እንመልከት፡፡

> የጉባኤውን ትኩረት ስቦ የነበረው ሌላው ድርጊት በእሳት የተለኮሰው መስቀል ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ እሳቱ የወንጌልን እሳት ወይም የመንፈስ ቅዱስን እሳት ለማሳየት እንደ ተለኮሰ እገምታለሁ፡፡ ሆኖም መጋቢው መስቀሉን ተሸክመው ቢያሳዩን ኖሮ አገልግሎት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ አይረሴ ትምህርት ባገኘን ነበር፡፡
>
> የነጻነት መዘዝ (ያልታተመ)

መቼም አንድ ጭንቅላቱ ያልታመመ ሰው ሌላው ሰው የጋለ መስቀል ተሸክሞ በማየት ትምህርት ለመውሰድ አይጠብቅም፡፡ ይህንን የጠየቃችሁት እውነት ስላልገባችሁ ከሆነ ጽሑፉን እንደገና እንድታነቡት አበረታታችኋለሁ፡፡

## <u>ወንድማዊ ራሮትን ማጣት (being insensitive)</u>

ከወንድም ጳውሎስ ፈቃዱ ጀርባ ህጸጹን የማይነግሩት ሰዎች እንዳሉ ባስተላለፋችሁት መልእክት ላይ "... ነገ እንዳያዝንባችሁ ..." ማለታችሁ የወንድማችን ነገ አሳዛኝ እንደ ሆነ ዛሬ ላይ አምናችሁ የተቀመጣችሁ ትመስላላችሁ፤ ይህም ልክ ነቢዩ ዮናስ የነነዌን ጥፋት እንደተጠባበቀው ይሆንባችኋል፡፡ ጽሑፋችሁን ወደ ማጠቃለል ስትቃረቡ ደግሞ፣ ገና በምጽአት ቀን ስለሚጠብቀው ፍርድ ታወጉታላችሁ፤ ምንም እንኳ በድኅል ብላችሁ ብታምኑ በሕይወት ያለ አማኝ የመመለስ ተስፋ እንዳለው ያለማወቅ ሳይሆን ይህ ወንድማዊ ራሮትን ማጣት ነው፡፡

## <u>ትሻል ሔዳ ትብስ መጣች</u>

ወንድም ጳውሎስ ፈቃዱ ምንም ሳንካ የሌለበት መልከ ሰብ አርኣያ መልአክ ነው የሚል ሙግት የለኝም፡፡ ለምሳሌ ከባድ ምጸቶችን ይጠቀማል፤ የጽሑፎቹ "ቶን" ጠንካራ ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ በበርካታ ጽሑፎቹ ለሠራቸው ስህተቶች እናንተ አንድ ጊዜ "እንጨኽ"


www.Ethiocross.com

ብላችሁ የተሳደባችሁት ስድብ እንኳን ክርስቲያን ማንም ያልደነዘዘ ሕሊና ያለው ሰው ሊያደርገው አይችልም። ስለዚህም ሥራችሁ ትሻል ሄዳ ትብስ መጣች እንደሚባለው ሆኗል።

## ሁሉን ዐውቃነት

ሁሉን ዐውቃነት መለኮታዊ በሆነው ዓለም የፈጣሪ ብቻ ሲሆን በልቦለዱ ዓለም ደግሞ የተራኪ (narrator) ነው። እውነት ቀመስ ልብወለድ ጻፍክ ያላችሁ ወንድሞቻችን፣ "እኛ ... ቀድሞውንም እንደዚህ እንደምትጽፍ እናውቅ ነበር"፤ በተጨማሪም ለሌሎች "ወደፊት እንዳያዘንባችሁ" እያላችሁ በመጻፋችሁ እናንተስ ሁሉን ዐውቃ የሆናችሁ አይመስላችሁም?

በአንጻሩ ደግሞ ማንም በቀላሉ ሊያውቀው የሚችለውን ነገር፣ ለምሳሌ ለአስተማሪነት የሚሆን ማንነትን ፈልገን አጥተንብሃል ትላላችሁ። ጳውሎስ መደበኛ ሥራው መምህር እንደሆነ ያላወቃችሁት ያ ሁሉን አውቃነታችሁ ስላላገዛችሁ ነው? ወይስ የምታውቁት ማወቅ የምትፈልጉትን ብቻ ስለሆነ ነው?

## የተፈለገ ቀዳዳ እና ያልተፈለገ ቀዳዳ

አንዳንድ ቀዳዳ ተፈልጎ ሊደረግ የሚችል ሲሆን፣ ለምሳሌ ልብሶች ቁልፍ (አዝራር) ለማስገቢያ ሆን ተብሎ ቀዳዳ ይሠራላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ግን አንዳንድ ነገሮች ለምሳሌ ልብስ በእርጅና ምክንያት ለቀደድ ይችላል። ስለዚህ ቀዳዳ በተመለከትን ቁጥር በስሕተት (ሳይፈለግ) ተቀዶ ከመሰለን ችግር ነው።

ለምሳሌ የማቅናት ወይስ ንቀት ጸሐፍት ወንድሞቻችን ጳውሎስ ቦንቦሊኖ ሲቀርብለት ቀዳዳውን ብቻ እንደሚያይ ገልጻችኋል። ቦንቦሊኖ እኮ ተፈልጉ የተደረገለት ቀዳዳ እንጂ ሞያ በማጣት ወይም ድክመት ሆኖ አይደለም እንደዚያ የሆነው።

## ጳውሎስ ፈቃዱ ማን ነው?

መጽሔት አንዱ የብዙሃን መገናኛ መንገድ ነውና ተደራሲው ለየቅል (Heterogeneous) መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም፣ ይህ እንደዚህ እያነጋገረ ያለ ሰው (ጳውሎስ ፈቃዱ) ማነው ብሎ የሚጠይቅ አይጠፋምና በተጨማሪም የ "ማቅናት ወይስ ንቀት?" ጸሐፍት ወንድሞቻችን "ማን ነህ አንተ?" ስትሉ ስለ ጠየቃችሁ አሁን ከያዝነው አጀንዳ አንጻር ብቻ መልስ ልስጥ:-

ጳውሎስን አንዳንዶቻችን በትርጉም ሥራዎቹ፣ ብዙዎቻችን ደግሞ በየመጽሔቱ ከምናነባቸው መጣጥፎቹ እናውቀዋለን። (ሰረዝ ከራሴ)

መጋቢ በቀለ ወ/ኪዳን

ጋሽ በቀለ ይህንን የተናገሩት፣ ጳውሎስ ፈቃዱ በጻፈው "ያልተንኳኩ በሮች" በተሰኘው መጸሐፍ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት በራሱ ተጠይቀው ነው። (ጳውሎስ መጽሐፉ ከመታተሙ በፊት የላከላቸው መጽሐፉ ጀርባ ላይ የሚጻፍ አስተያየት (blurb) እንዲጽፉለት ሳይሆን፣ እርማት እንዲሰጡበት እንደ ሆነ ተሻሽሎ በድጋሚ በታተመው


www.Ethiocross.com

በዚሁ መጽሐፍ ጀርባ ላይ ተጽፎ ይገኛል፤ "ሳልጠየቅ የጻፍኩት ስለሆነ ..." ብለዋል መጋቢው።)

አንባቢ የሆነ ወንድም ይህንን ሰው የሚያውቀው ከመስከረም 2002 ዓ.ም በፊት ነው ማለት ነው።

ጳውሎስ አራሚ የሌለው አሊያም ቢያርሙትም የማይሰማ እንደ ሆነ ተገልጿል። እስኪ ነገሩን በምሳሌ እንመልከተው፦

"ያልተንኳኩ በሮች" በሚለው መጽሐፉ ላይ ለጽሑፉ እርማት በመስጠታቸው ስማቸው የተዘረዘረ ወገኖች ልጁ ለእርማት የቀና ልብ እንዳለውና አቅኚም እንዳለው ዋቢ ይሆናሉ። በተጨማሪም መጽሐፉ ተሸሽሎ ለሁለተኛና ለሦስተኛ ጊዜ መታተሙ ደግሞ ሌላው አብነት ነው።

በማቴቴስ መጽሔት ቁ.10 ላይ "ያልተጻፉ ጥቅሶች" በሚል ርእስ ባስነበበው ጽሑፉ ስሕተት በመሥራቱ መጋቢ ስሜ ታደስ ማረማቸውንና ለእኚሁ መጋቢ መታሰቢያነት መጽሔቱ አዲስ በከፈተው "ተሳስቼ ነበር!" የሚል አምድ ላይ ስለ መሳሳቱ ደፍሮ መጀመሪያ የጻፈ (ice breaker) ጳውሎስ ፈቃዱ ነው። በዚሁ ጽሑፉ "ምክንያታዊ ተቃዋሚዎቼንና ምክንያታዊ ደጋፊዎቼን አመሰግናለሁ (ከጭፍን ደጋፊዎቼና ከጭፍን ተቃዋሚዎቼ ፈጣሪ እንዲጠብቀኝ ግን ጸልዩልኝ)።" ማለቱ ይታወሳል። እኔም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ "የነጻነት መዘዝ"ን ጨምሮ በሌሎቹም ጽሑፎቹ ተሳስቷል ብዬ የማምነው ነገር ሲኖር ከመናገር በአንዳች ምክንያት ተጥቆቤ አላውቅም።

## ሥነ ጽሑፋዊ ግድፈቶቻችሁ

የጽሑፋችሁ መነሻ የሆናችሁ ወንድም የሰው መልካምነትን መናገር እንደሚቸገር ላቀረባችሁት ሙግት ዋቢ የሆናችሁ የደበበ ሰይፉ ግጥም ካነሣችሁት ርእስ ጋር ምንም ዐይነት ተያያዥነት የለውም። ግጥሙ የሚያጠነጥነው ስለ ስስት ነው። (ለነገሩ ከሰማነው ቆየን ማለታችሁ ይታወሳል)። ይህንን ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ ለጽሑፋችሁ ግብኣት የተጠቀማችሁት ያለቦታው ነው።

ያለ ቦታቸው የገቡ (ዐውዳዊ ፍች የሌላቸው) ተረቶች ሌሎቹ የጽሑፋችሁ ሳንካዎች ናቸው። ለምሳሌ "ይሉኝን ባልሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ" የሚለው ተረት ትክክለኛ አባባሉ "ይሉኝን በሰማሽ" ሲሆን፣ ያለቦታው የተደነቀረ ነው።

"የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" ስትሉ ተርታችሁ ነበረ፤ ይህ ተረት እንዲህ ሳይሆን "የሚያጠግብ እንጀራ ..." ነው። አንድ በሕይወት ያለ ሰው ላይ የስድብ ውርጅብኝ ስታወርዱ ማለትም እንዲህ ዐይነት ሥሡ (delicate) ጉዳይ ሲነሣ መልሶ ሥሡ (sensitive) መሆን ያስፈልጋል።

የቁጥርና የመደብ አለመስማማት ደግሞ ሌላኛው ሥነ ጽሑፋዊ ግድፈታችሁ ነው። አንዴ ለራሱ ለጳውሎስ በቀጥታ የተጻፈ ይሆንና (አንተ በማለት) ደግሞ በሌላ ስፍራ ላይ ለሌላ የተጻፈ (እርሱ የሚል) ይሆናል። ይህንን ስሕተት ደግሞ ራሱ ጳውሎስ በዚሁ መጽሔት ከዚህ በፊት ለተጻፈበት ትችት "መጻፍ ራስን ማጋለጥ ነው" በሚል ርእስ ምላሹን በ"ሆዶስ" መጽሔት ሲያቀርብ ከተቻቸው ነገሮች መካከል አንደኛው ነው። ያኔ የተነገረ ስሕተት አሁንም ሳይስተካከል መገኘቱ የመጽሔቱ አዘጋጆች ለእርምት ያላቸውን ነገር ነው የሚያሳየው።


www.Ethiocross.com

ቋንቋ የጥቅል መጠርያ ሲሆን በድፍኑ ጨዋ ቋንቋ የሚባል ወይም ባለጌ ቋንቋ የሚባል የለም። በአንድ ቋንቋ ውስጥ ጸያፍ ቃላት ሊኖሩ ይችላሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ ጥሩ ቃላት ይኖራሉ።

## ለጌሜም መጽሔት ዝግጅት ክፍል

በመጽሔታችሁ የመጀመርያ ገጽ ላይ የወንጌላውያን አማኞች እምነትና የአስተሳሰብ ሥርዐት የምታንጸባርቅ መንፈሳዊ የግል መጽሔት ትላላችሁ። … ጀርባ ላይ የተጣበቅህ ቅማል፣ ተራ፣ ትንሽ፣ ስድ፣ ወጥ እረገጥ አጉራ ዘለል፣ ክፍት አፍ (Paraphrase የተደረገ ነው) … የሚል ገለጻ የወንጌላውያን አማኞች እምነትና የአስተሳሰብ ሥርዐት ነጸብራቅ ነው እንዴ? በመጽሔት ሥራ ላይ በስፋት የሚጠቀሰው አባባል (ከመልእክተ እገሌ በስተቀር በዚህ መጽሔት የሚወጡ ጽሑፎች የመጽሔቱን አቋም ላያንጸባርቁ ይችላሉ) ጌሜም ላይ የለምና ስድቡ የመጽሔቱም አቋም ነው ማለት ነው። እጅጉን የሚገርመው ደግሞ ከሌሎች መጽሔቶች በተለየ መጋቢዎችና ወንጌላዊ በኅብረት አዘጋጅ በሆኑበት እንዲህ ያለ ስሕተት መፈጠሩ ነው።

መጋቢ ዝናው ደነቀ፣ ዘማሪ ኤፍሬም ዓለሙ በቅርቡ ለሕዝብ ባቀረበው የቪሲዲ ሥራው ላይ አንድ ከእስራት ነጻ ስለ ተፈታ ወንድም በሚሰጡት ምስክርነት ጉዳዩን እንደ እግዚአብሔር ሰውና እንደ ጋዜጠኛ እንደተከታተሉት ይገልጻሉ እርሶ ማኔጂንግ ኤዲተር ሆነው በሚሠሩበት መጽሔት ከላይ የተገለጹትን ዐይነት ጸያፍ ቃላት የያዘ ጽሑፍስ ሲያስተናግዱ ጉዳዩን "እንደ እግዚአብሔር ሰውና እንደ ጋዜጠኛ" አልተመለከቱትም? (መቼም ይሄን ሁሉ የምለው እርሶ ጽሑፉን ካዘጋጁት ወንድሞች ውስጥ እንደሌሉ በማመን ነው።)

የዚህ ወንድም ጽሑፎች በመጽሔታችሁ መነበብ ከጀመሩ ቆዩ፤ በአንጻሩ ደግሞ በእርሱ ላይ አሉታዊ ነገርን ለያዙ ጸሐፍት መጽሔታችሁ ማስወንጨፊያ በመሆን እያገለገለች ነው። የሚገርመው ደግሞ እርሱ በመጽሔታችሁ ይሳተፍ በነበረበት ጊዜ አንዴም በውጪ ሽፋን ላይ የእርሱ ጽሑፍና ስሙ በአንድነት ተገልጾ ሳያውቅ ስለ እርሱ የጭቃ ጀራፍ ያነሡ ጸሐፍት ደግሞ በውጪ ሽፋን ላይ የማስተዋወቅ ዕድሉን አግኝተዋል። ይህን ከሚዛናዊነት አንጻር እንዴት ትመለከቱታላችሁ?

ከዚህ በተጨማሪም "ሰይፍህን ወደ ሰገባ አስገባ" በሚለው ከዚህ በፊት ባሳተማችሁት ጽሑፍና "ማቅናት ወይስ ንቀት" በሚለው በአሁኑ ጽሑፍ መካከል ያለው ተመሳስሎ፡-

- ሁለቱም ጽሑፎች አንድ ግለስብ ላይ ያነጣጥራሉ
- በሁለቱም ጽሑፎች ላይ የጸሐፊዎቹ ማንነት አልተገለጸም
- ሁለቱም ጽሑፎች በአንድ መጽሔት ላይ ነው የታተሙት
- ሁለቱም ጽሑፎች በውጪ ገጽ ላይ የመተዋወቅ ዕድል አግኝተዋል
- ሁለቱም ሁለቱም ጽሑፎች ተመሳሳይ እንከኖች ይታዩባቸዋል

ስለዚህ የሁለቱም ጽሑፎች ጸሐፊ አንድ ሰው ሊሆን እንደሚችል አቅጣጫ ይጠቁማል።

ጳውሎስ በድረ ገጽ ያሰራጨውን ጽሑፍ ለማንበብ ጽሑፉን በኢንተርኔት አሊያም ቅጂውን ማግኘት መፈለግን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ ቢያንስ ስለ ጉዳዩ ትንሽ መስማት


www.Ethiocross.com

ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊ ቁም ነገርን ፈልጎ ገንዘብ አውጥቶ መጽሔት ገዝቶ ያለ ውጼታው በገዛ ገንዘቡ ስድብ እንዲያነብ አንባቢን መጋበዝስ ምን ይሉታል?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጳውሎስ ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ በተለያዩ መጽሔቶች ያቀረባቸው ሲሆኑ በእርግጥ ሐሳብ ላይ ወይስ ሰው ላይ ያመዝናል ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ፡፡

ማቴቴስ ቁ. 10 መጋቢት/2001 ዓ.ም "ሞትን ማን ያመልጣል?" ስለ ሞት ብዙ ተጽፏል፡ ተገጥሟል፤ ተብሏል፡፡ በመጀመርያው አዳም ምክንያት ሰው የመጣበትን ሞት አምላክ ሆኖ ሳለ ሰው ሆኖ ሞትን በገደለው ጌታ ሞትን (ዘላለማዊውን) ያመልጣል፡

ሆዶስ መጋቢት - ግንቦት 2001 ዓ.ም "መጻፍ ራስን ማጋለጥ ነው" ሆዶስ ቁ.1 ይዘቱ ስንጽፍ ራሳችንን ወይንም ችሎታችንን እናሳያለን የሚል ነው፡፡ይህንን ጽሑፍ ከጻፍኩ በኋላም አስቀድሜ ለጌሴም መጽሔት አዘጋጅ ሰጥቻቸው እንደ ነበር መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ይህንንም ያደረግሁት ጉዳዩ የተነሣው እዚያው በመሆኑ ምላሹም እዚያው እንዲወጣ ሙያው ስለሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን፣ የመጽሔቷንም ሚዛናዊ መሆን አለመሆን ማየት ስለፈለግሁና በተከሰስሁበት ቦታ ራሴን የመከላከል መብት እንዳለኝ እንደሚገነዘቡ በማሰብም ጭምር ነበር፤ ሆኖም አዘጋጁ ጽሑፌን ሊያወጡት እንደማይፈልጉ ስላሳወቁኝ ወደዚህ መጥቻለሁ፡፡

ማቴቴስ ቁ. 11 ሐምሌ /2001 ዓ.ም *"ያልተጻፉ ጥቅሶች"* ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተወሰዱ ተደርገው በየመድረኮቻችን የምንሰማቸው ነገር ግን ገሚሱን በዘልማድ፣ ገሚሱን ከትውፊት፣ ገሚሱን ከቅብብሎሽ … የመጡን ምንጭ አልባ ጥቅሶቻችንን እንተውና መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን እንበል፤ አክብሮ የተጠራውን አክብረን እንጥራ፡፡

ቃና ዘገሊላ ቁ.005 ነሐሴ 2001 ዓ.ም *"ባለቤቴ የሚለው ቃል ያስፈራኛል!"* በአማርኛ ባለቤቴ የሚለው ቃል ከሚወክላቸው ሐሳቦች መካከል የግል ንብረትነት አንዱ ሲሆን፣ የትዳር ጥንዶች አንዳቸው ያንዳቸው ባል ወይም ሚስት መሆናቸውንም ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ቃሉ የወከለውን ሐሳብ ያህል ሳይሆን፣ በተግባር የሚታየው እንደውም ተቃራኒውን እስኪመስል የጋራ ነገር የማይታይባቸው ጥንዶች አሉና የቃሉ ፍች ያስፈራኛል፡፡

ቃና ዘገሊላ ቁ.006 *"የማልወደው አሰልቺ ጥያቄ"፤* ጥያቄ እንደው ጥያቄ ስለሆነ ብቻ አልወድም ደግሞም አልጠላም፡፡ ነገር ግን ለምን አታገባም? የሚለው ጥያቄ ሰው ያላገባበት ወይንም የማያገባበት ብዙ ምክንያት ስለሚኖር አሰልቺ ከሆኑብኝ ጥያቄዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

ማቴቴስ ቁ. 12 ጥቅምት 2002 ዓ.ም *"ጸሎታችንን ራሳችን ብንመልሰው?!"* ለምንዱባን የመድረስ ኀላፊነት የፈጣሪ ብቻ የመሆኑን ነገር ሳይታወቀን ተስማምተንበት የመድገም ያህል ለወጉ ከምናደርስው ጸሎት ወጥተን እኛው ብንደርስላቸውስ?

ማቴቴስ ቁ. 13 ታህሳስ /2002 ዓ.ም *"የእኔዎቹ ስሕተቶች"* ጸሐፊው በሌሎች ተነግረውት ራሱም አስተውሎ የተጸጸተባቸውን ስሕተቶቹን የተናዘዘባው ጽሑፎች ናቸው፡፡

**ማጠቃለያ**

ሰዎች ከህሊና ጋር የተፈጠርን በመሆናችን በጋራ ትክክል ነው ወይም አይደለም እያልን በጋራ የምንስማማበት ነገር አለ፡ አንዳንድ ነገሮች ከሕሊና ዳኝነት አንጻር


www.Ethiocross.com

በየትኛውም ክፍለ ዓለም፣ ክፍለ አህጉር፣ ሀገር፣ ዘር፣ ቀለም፣ ቋንቋ ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል፤ ለምሳሌ ጸያፍ ንግግር።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ የአንዳንድ ነገሮች ትክክለኝነት ደግሞ አንጻራዊ ይሆናል። ለአብነት ያህል በአንዱ ሃይማኖት ልክ የሆነው በሌላው ስሕተት ሊሆን ይችላል። እነዚህ ልዩነቶች ግን መረን አልለቀቁንም። ዓለም ሕግ አላት፤ ሞያዎች (disciplines) የሞያ ሥነ ምግባር አላቸው። ከእነዚህም መካከል ጋዜጠኝነት አንዱ ነው። ይህ የሞያ ዘርፍ በአሁኑ ጊዜ ካሉ ሞያዎች ውስጥ እጅግ መሥዋዕትነትን (የሕይወትንም ሳይቀር) እየጠየቀ ያለ ሞያ ነው። የዚህ የሞያ ዘርፍ የሥነ ምግባር ደንብ (Code of Ethics) ከሆኑት ውስጥ አንዱ Avoid Your Prejudice አንዱ ነውና እንደው እንደው ህልሙን እንደሚያወራ አንድ ሰው "ይመስለኛል፤ እጠረጥራለሁ፤ አልጠራጠርም" እያሉ መጻፍ ሞያውን ማርከስ ይሆናል። በተጨማሪም ትክክለኝነት (accuracy)፣ ሚዛናዊነት (balance)፣ ግልጽነት (clarity)፣ ABC የሞያው መለያ ናቸውና ለሞያ መገዛት አንድም ጨዋነትን፣ አንድም ብቃትን ያሳያል።

<u>ማስታወሻ</u>

1. ዳዊት ጸጋዬ፤ አዲስ አድማስ ጋዜጣ



www.Ethiocross.com